# የፕሮስቴት አልትራሳውንድ እና ባዮፕሲ

*እንዴት እንደሚዘጋጁ እና ምን እንደሚጠበቅ*

*ይህ ጽሑፍ ለፕሮስቴት አልትራሳውንድ እና ባዮፕሲ ምርመራ እንዴት መዘጋጀት እንደቢገባ ይገልጻል። እንዴት እንደሚከናወን፣ ስለ ስጋቶቹ እና ውጤትዎን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ያትታል።*

***የዚህን ጽሑፍ ዲጂታል ቅጂ ለማግኘት በስልክዎ ካሜራ ይመልከቱ።***


**የፕሮስቴት አልትራሳውንድ እና ባዮፕሲ ቀጠሮ የሚከተለው መርሐግብር ተይዟል፡-**

- ❑ **የፕሮስቴት ኦንኮሎጂ ክሊኒክ**, በሰርጀሪ ፓቪሊዮን፣ ዩ ደብሊው ሜዲካል ሴንተር - ሞንትሌክ ካምፓስ በሚከተለው አድራሻ ይገኛል፤ 1959 N.E. Pacific St., Seattle, WA 98195
- ❑ **የወንዶች ጤና ማዕከል ዩ ደብሊው ኤም ሲ**, UWMC - Roosevelt, 4245 Roosevelt Way N.E., Seattle, WA 98105.
- ❑ **ኖርዝዌስት ሆስፒታል** – ማክሙረይ ዩሮሎጂ፣ 1536 N 115th St., Suite 300
- ❑ **ዩ ደብሊው ኢስትሳይድ ስፔሻሊቲ ሴንተር፣** 3100 Northup Way, Bellevue, WA 98004

እለት: ____________ ቀን: _______________ የመድረሻ ጊዜ: _________

**የፕሮስቴት አልትራሳውንድ እና ባዮፕሲ ምንድን ነው?**

የፕሮስቴት አልትራሳውንድ እና ባዮፕሲ የፕሮስቴት ካንሰርን ለመመርመር አንድ ላይ የሚደረጉ ምርመራዎች ናቸው። እነዚህ ምርመራዎች በዶክተርዎ ቢሮ ውስጥ ሊደረጉ ይችላሉ። አልትራሳውንድ ሐኪምዎ ፕሮስቴትዎን እንዲያዩ ያስችላቸዋል። በባዮፕሲው ውስጥ፣ ዶክተርዎ የፕሮስቴትዎን ቲሹ ናሙናዎችን ይሰበስባል።



***ይህንን ጽሑፍ ካነበቡ በኋላ ስለ ፕሮስቴት አልትራሳውንድ እና ባዮፕሲዎ ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይነጋገሩ።***

## ይህ ምርመራ ለምን ያስፈልገኛል?

የሚከተሉት ከሆኑ እነዚህን ምርመራዎች ሐኪምዎ ያዘዙልዎት ይሆናል፡

- የደም ምርመራ ውጤትዎ ከፍ ያለ ወይም እየጨመረ ያሚሄድ የፕሮስቴት የተወሰነ አንቲጅን (ፒ ኤስ ኤ - PSA) ካለው። ፒ ኤስ ኤ የፕሮስቴት ዕጢ የሚያመነጨው ፕሮቲን ነው። ከፍተኛ የ ፒ ኤስ ኤ ደረጃዎች ከካንሰር ጋር የተቆራኙ ናቸው።
- የፕሮስቴትዎ የፊንጢጣ ምርመራ ውጤት መደበኛ ያልሆነ ከነበረ።

## ለዚህ ምርመራ እንዴት እዘጋጃለሁ?

ለእነዚህ ምርመራዎች ለመዘጋጀት ማድረግ **ያለብዎት** እነዚህ ናቸው፡

- ከምርመራዎ በፊት ባሉት ሰባት ቀናት ምንም አይነት ደም የሚያቀጥን መድሃኒት አይውሰዱ። ከእነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹ አስፕሪን፣ አይቡፕሮፌን (አድቪል፣ ሞትሪን)፣ ዋርፋሪን (ኮማዲን) እና ክሎፒዶግሬል (ፕላቪክስ) ናቸው። በመደበኛነት እነዚህን ወይም ሌሎች ደም ማቅጠኛዎችን የሚወሰዱ ከሆነ፣ አስፈላጊውን እንድንመክርዎ ለነርስዎ ይንገሩ።

- ሐኪምዎ የሦስት አንቲባዮቲክ መድኃኒቶች ማዘዣ ይሰጥዎታል፡-
  - ይህንን የመድኃኒት ማዘዣ ወደ ፋርማሲዎ ወስደው ያስሞሉ።
  - የመጀመሪያውን ክኒን ከአልትራሳውንድ እና ባዮፕሲ በፊት ባለው ቀን ከምሽቱ 8፡00 ሰዓት ላይ ይውሰዱ።
  - ከዚያም እስኪያልቁ ድረስ በየ12 ሰዓት ልዩነት 1 ኪኒን ይውሰዱ።
- *ፍሊትስ ኢኔማን* ከመድኃኒት ቤት ይግዙ። ያለ ሐኪም ማዘዣ ሊገዙት ይችላሉ (over the counter)። የፕሮስቴት አልትራሳውንድ እና ባዮፕሲ ከማድረግዎ በፊት ባለው ምሽት ኢኔማውን ይጠቀሙ። በፍሊት መያዣው ላይ ያሉትን መመሪያዎች ይከተሉ።
- የተለመዱ ምግቦችን መመገብ ይችላሉ። እባክዎን በምርመራዎ ቀን እንደወትሮው መመገብዎን እንዳያቋርጡ።

**እባክዎን ያስታውሱ፡ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ከአልትራሳውንድ እና ባዮፕሲ ቀጠሮዎ በፊት ካላደረጉ፣ የእርስዎን ምርመራዎችዎን ወደሌላ ጊዜ ማስተላለፍ ሊኖርብን ይችላል።**

## በምርመራ ጊዜ ምን ይፈጠራል?

- ሲደርሱ ወደ ምርመራ ክፍልዎ እንወስድዎትና የሐኪም ቤቱን ልብስ እንዲቀይሩ እንጠይቅዎታለን። ሐኪምዎ ቀላል የፊንጢጣ ምርመራ ያደርጋልዎታል።
- በመቀጠል ትንሽ መመርመሪያ (በመጠን እና በቅርፁ ጣት የሚመስል መሳሪያ) በፊንጢጣዎ ውስጥ ይደረጋል። የአልትራሳውንድ ሞገዶች የፕሮስቴትዎን ምስሎች ይሰጡናል። ስለ ፕሮስቴትዎ የተለያዩ ብዙ እይታዎችን እንዲሰጠን ዶክተርዎ መመርመርያውን በትንሹ ያንቀሳቅሱታል። ሕመም አይሰማዎትም።
- በመቀጠል፣ ዶክተርዎ በጣም ቀጭን መርፌን በመጠቀም ማደንዘዣ መድሃኒት ወደ ፕሮስቴትዎ ውስጥ ይወጋል። ዶክተርዎ ለካንሰር ምርመራ የሚሆን 12 በጣም ትንንሽ የቲሹ ናሙናዎችን ይወስዳሉ። ብዙውን ጊዜ ይህ (ሂደት) ሕመም የለውም።
- አጠቃላይ ምርመራው 20 ደቂቃ ያህል ይወስዳል።

## ከምርመራ በኋላ ምን ልጠብቅ?

- ከምርመራዎ በኋላ ለተወሰኑ ሰዓታት በፊንጢጣ አካባቢዎ ላይ ትንሽ የሕመም/ያለመመቸት ስሜት ሊኖርዎት ይችላል።
- **ከባዮፕሲው ምርመራ በኋላ ለአንድ ሳምንት በሽንትዎ እና በሰገራዎ ውስጥ የተወሰነ ደም ማየት የተለመደ ነው።** በአንዳንድ ሁኔታዎች በሽንትዎ ውስጥ ያለው ደም እስከ 1 ወር ድረስ ሊቆይ ይችላል። ክሊኒኩን ለቀው ከመሄድዎ በፊት በሽንትዎ ውስጥ ብዙ ደም እንደሌለዎት ለማረጋገጥ ሽንት እንዲሸኑ እንጠይቅዎታለን።
- በወንድ የዘር ፈሳሽዎ ውስጥ ለ2 ወራት የሚዘልቅ ደም መኖር የተለመደ ነው።

## የእነዚህ ምርመራዎች አደጋዎች ምንድን ናቸው?

እነዚህ ምርመራዎች አንዳንድ አደጋዎች አሏቸው። ጥቃቅን አደጋዎች በሽንትዎ፣ በወንድ የዘር ፈሳሽዎ እና በሰገራዎ ውስጥ የሚኖረው ደም ነው። የፕሮስቴትዎ ወይም የሽንት ቱቦዎ ኢንፌክሽንም ሊገጥመውም ይችላል።

ከሚከተሉት ምልክቶች አንዱ ካለዎት ሐኪምዎ ጋር ይደውሉ:

- ከ 101°F (38.6°C) በላይ የሆነ የሰውነት ሙቀት
- ብርድብርድ ማለት
- ብዙ ሕመም
- ብዙ ወይም ለረጅም ጊዜ ደም መፍሰስ

## የምርመራ ውጤቴን እንዴት አገኛለሁ?

የምርመራ ውጤትዎ እንደደረሰን እንደውልልዎታለን። ውጤቱ በአንድ ሳምንት ውስጥ ይደርሳል።

በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ ከኛ ካልሰሙ ይደውሉልን እና ውጤትዎን እናረጋግጣለን።

### ጥያቄዎች?

ጥያቄዎችዎ አስፈላጊ ናቸው። ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉዎት ሐኪምዎን ወይም የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይደውሉ።

<u>የፕሮስቴት አንኮሎጂ ክሊኒክ</u>

**በስራ ቀናት ከጥዋቱ 8:30 እስከ ቀኑ 5:00፣ Weekdays 8:30 a.m. to 5 p.m.:** በ 206.598.6088 ላይ ይደውሉ።

**ከስራ ሰዓታት በኋላ እና ቅዳሜና እሁድ ወይም በበዓላት ቀን:** በ 206.598.6190 ላይ ይደውሉ እና ሬዚደንት ኦንኮሎጂስትን እንዲያገናኙዎ ይጠይቁ።

<u>የወንዶች የጤና ማዕከል</u>

**በስራ ቀናት ከጥዋቱ 8:30 እስከ ቀኑ 5:00፤** 206.598.6358 ላይ ይደውሉና 2 ትን ይጫኑ።

**ከስራ ሰዓታት በኋላ እና ቅዳሜና እሁድ ወይም በበዓላት ቀን፣** ነርስ ለማነጋገር ተመሳሳይ ቁጥር ይደውሉ። ለአስቸኳይ ጉዳዮች ተረኛው የኡሮሎጂ ሐኪም ለደወልላቸው ይችላል።

<u>ኖርዝዌስት ሆስፒታል</u>

**በስራ ቀናት ከጥዋቱ 8:30 እስከ ቀኑ 5:00፤** 206.668.5212 ላይ ይደውሉና 2 ትን ይጫኑ።

<u>ዩ ደብሊው ኢስትሳይድ ስፔሻሊቲ ማዕከል</u>

**በስራ ቀናት ከጥዋቱ 8:30 እስከ ቀኑ 5:00 እና ቅዳሜ ከቷቱ 9:00 እስከ 8:00:** በ 425.646.7777 ላይ ይደውሉ።

© University of Washington Medical Center
Published PFES: 2009, 2014, 2020, 2025
Clinician Review: 01/2025
Reprints on Health Online: https://healthonline.washington.edu

# Prostate Ultrasound and Biopsy

*How to prepare and what to expect*

UW Medicine
UNIVERSITY OF WASHINGTON MEDICAL CENTER

*This handout explains how to prepare for prostate ultrasound and biopsy. It includes how they are done, risks, and how to get your results.*

***Scan with your phone camera for a digital copy of this handout.***

### Your prostate ultrasound and biopsy are scheduled at:

- ❑ **Prostate Oncology Clinic**, 1st floor of the Surgery Pavilion, UW Medical Center - Montlake campus, 1959 N.E. Pacific St., Seattle, WA 98195
- ❑ **Men's Health Center**, UWMC - Roosevelt, 4245 Roosevelt Way N.E., Seattle, WA 98105.
- ❑ **Northwest Hospital** – McMurray Urology, 1536 N 115th St., Suite 300
- ❑ **UW Eastside Specialty Center**, 3100 Northup Way, Bellevue, WA 98004

Day: ___________ Date: ______________ Arrival Time: ________

## What is a prostate ultrasound and biopsy?

A prostate ultrasound and biopsy are tests done together to check for prostate cancer. These tests can be done in your doctor's office. The ultrasound allows your doctor to see your prostate. In the biopsy, your doctor will collect tissue samples of your prostate.



***Talk with your healthcare provider if you have any questions about your prostate ultrasound and biopsy after reading this handout.***

## Why do I need these tests?

Your doctor may have ordered these tests if you:

- Have a high or rising *prostate specific antigen* (PSA) blood test. PSA is a protein the prostate gland produces. High PSA levels are linked to cancer.
- Had a rectal exam of your prostate with abnormal results.

## How do I prepare for these tests?

These are things you **must** do to prepare for these tests:

- Do **not** take any blood-thinning medicines for 7 days before your tests. Some of these are aspirin, ibuprofen (Advil, Motrin), warfarin (Coumadin), and clopidogrel (Plavix). If you normally take these or any other blood thinners, tell your nurse so we can advise you about this.

- Your doctor will give you a prescription for 3 antibiotic pills:
  - Fill this prescription at your pharmacy.
  - Take the first pill at 8 p.m. the night before your ultrasound and biopsy.
  - Then, take 1 pill every 12 hours until they are gone.
- Buy a Fleets enema at the drugstore. You can buy it without a prescription (over the counter). Use the enema the night before your prostate ultrasound and biopsy. Follow the directions in the Fleets box.
- You may eat your normal foods. Please do **not** skip meals the day of your tests.

**Please note: If you do not do all these things before your ultrasound and biopsy appointment, we may need to reschedule your tests for another day.**

## What will happen during the tests?

- When you arrive, we will take you into your exam room and ask you to change into a gown. Your doctor will do a simple rectal exam.
- Next, a small *probe* (a device that is finger-like in size and shape) will be placed into your rectum. Ultrasound waves will give us pictures of your prostate. Your doctor will move the probe slightly to give us many different views of your prostate. You will not feel pain.
- Next, your doctor will use a very thin needle to inject a numbing medicine into your prostate. Your doctor will take about 12 very small tissue samples to test for cancer. Normally, this is not painful.
- The entire test will take about 20 minutes.

## What can I expect after the tests?

- You may have a small amount of tenderness in your rectal area for a few hours after your procedure.
- **After the biopsy, it is normal to see some blood in your urine and stool for 1 week**. In some cases, blood in your urine may last for up to 1 month. Before you leave the clinic, we will ask you to urinate to make sure you do not have too much blood in your urine.
- Blood in your semen is common for 2 months.

## What are the risks of these tests?

These tests have some risks. Minor risks are blood in your urine, semen, and stool. Infection of your prostate or urinary tract may also occur.

Call your doctor if you have any of these symptoms:

- Fever higher than 101°F (38.6°C)
- Chills
- A lot of pain
- A lot of bleeding or bleeding that lasts a long time

## How do I get my test results?

We will call you as soon as we get your test results. We should get them in about 1 week.

If you have not heard from us in 7 working days, please call us and we will check on your results.

### Questions?

Your questions are important. Call your doctor or healthcare provider if you have questions or concerns.

**Prostate Oncology Clinic**

**Weekdays 8:30 a.m. to 5 p.m.:** 206.598.6088.

**After hours and on weekends or holidays, call** 206.598.6190 and ask for the resident on call for Oncology to be paged.

**Men's Health Center**

**Weekdays 8 a.m. to 5 p.m.:** 206.598.6358, press 2.

**After hours and on weekends or holidays**, call 206.598.6190 and ask for the resident on call for Oncology to be paged.

**Northwest Hospital**

**Weekdays 8 a.m. to 5 p.m**.: 206.668.5212 and press 2

**After hours and on weekends or holidays**, call the same number to speak to the nurse. For urgent issues, the Urology doctor on call may be paged.

**UW Eastside Specialty Center**

**Weekdays 7 a.m. to 5 p.m.:** 425.646.7777.

© University of Washington Medical Center
Published PFES: 2009, 2014, 2020, 2025
Clinician Review: 01/2025
Reprints on Health Online: https://healthonline.washington.edu